# ምዕራፍ ፲፫

## የመታሰቢያ ልዩ ልዩ ግጥሞች

### ታሪኩ አይሞትም !!

ያ ልበ ኩሩ የወኔው መጠን
የወንድነቱ ጥራት ሲመዘን
ኃይሉ ሲለካ ግብሩ ሲተመን
በጦር ሰውነት በሙያ ልኩ
ታላቅ ነውና፣ ሁሌም ያበራል ጀግናው ታሪኩ::

የጀግኖች ጀግና ክብር የወደደ
ለግል ጥቅም ያልተዋረደ
የተፋለመ ለዳር ድንበሩ
ያልተደፈረ ሀሞተ ኩሩ
የሞራል ውርደት የተጠየፈው
በታማኝነት ፀንቶ ያለፈው
ሞቱ ቢመርም ሥራው ያኮራል
በታሪክ መድረክ ቆሞ ያበራል::

ያስተማረውን መይሣው ካሣ
ሀቅ ተግባሩን ሰንደቅ ያነሳ
ስለ አገሩ ክብር የተቃጠለ
ሕልፈት በኩራት የተቀበለ
ከማዕዘን ደንጊያው፣ ከናደው ጉራ፣ ከሠራዊቱ
ሰርጾ የነበር ንፁህ ስሜቱ





ጉልቶ ይታያል በሥራው ፋና
ታሪኩ ሁሌም ሕያው ነውና::

በእናት አገሩ ስም እንደማለ
ለሙያው ክብር እንደታገለ
ምንደኛን ጠላት እንደመተረ
አስመሳይ ዋሾን እንዳስሸበረ
በተንኮል ብልሃት በግፍ ቢሰዋ
ቢጉነጭ እንኳ መራሩን ጽዋ
ጀግናው ታሪኩ ሀውልት ሆኖ
እንደ አባ ታጠቅ ይኖራል ገኖ::

---

ለብ/ ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔና የማዕዘን ደንጊያ ለነበረው
ለናደው ዕዝ ሠራዊት መታሰቢያ ተጽፎ መጋቢት 1980
በለገዳዲ ሬዲዮ ጣቢያ የተነበበ::
በወቅቱ በግጥሙ መተላለፍ በሬዲዮ ጣቢያው ላይ
ተግሣጽና ማስጠንቀቂያ ደርሷል፡

## ጊዜም ጀግና እንጂ ነው!!

*የታወረ አመራር እጁን በእጁ ቆርጦ
ከማይወጣበት ማጥ እንደገባ ሰምጦ
ተናገረ ጠላት በለስ ቀንቶት ገዱን
ታሪኩ መውደቁን፣ የናደው ማዕዘን ራስ ፣
ምገቡ መናዱን::*

*ናደው አልተናደም፣
ታሪኩም አልሞተም ተሳሳተ ጠላት
እነሱስ ሠርገዋል በወገን ልብ ውስጥ፣
በፍቅር በሙላት::*

*እርግጥ ነው በትግል ጥሉ መውደቅ አለ
የጦር ውሎ ወግ ነው በእውነት የተኳለ::
ለዓላማው ለዕምነቱ የወደቀ ወድቆ
ሥጋውን አርግፎ አጥንቱን አድቅቆ
ሞት አያግደውም፣
በመንፈስ ይጓዛል ጀግና ዘመን ዘልቆ::*

*ጀብዱ ሲመረመር የፍልሚያ ገመና
ጊዜም ጀግና እንጂ ነው፣ መች ሰው ብቻ ጀግና::
ጊዜ የሰጠው ቃል ድንጋይ እንደሚሰብር
ቀን ያነሳው ትንሽ ያበላሻል ነገር::*

*እንደ ተራ ተርታ ቅብብሉሽ ሂደት
ድልና ፍስሀ ዝናና ጀግንነት
ጊዜ ባቀበለው እርካብና ብልሃት
የሚለዋወጥ ነው ወድቆ እንደ መነሳት::*

*የመለያየትን ዕኩይ መንፈስ ጫና
ገርስሶ ለመጣል ወኔውን ያፀና
እንደ ቅዱስ ሙሴ ሰላም የማለደ
ማ ይሙት ታሪኩ፣ ናደው ዕዝ ተናደ::
ሆኖም አልታወቀ ወደፊትም አይሆን
ታሪክ ሞተ ብሎ ደምድሞ መወሰን::*






*አለማጤን እንጂ ነገርን በስልቱ
የማይናወፀው፣
ፍቅር የቀረፀው፣
በወገን ልብ ውስጥ ያበራል ህውልቱ
እንደ አባ ታጠቅ ስም እንደ አርማ ሰንደቁ
ታሪኩ፣ ናደው ዕዝ፣ ያበራሉ እንደ ዕንቁ::*

*****

*የካቲት 7/ 1981 ዓ.ም.
በፀሐይ መልአኩ
ለ1ኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ የተጻፈ*



*‹‹ በ1969 ዓ.ም ኃይል ለማጠናከር የእናት አገር የክተት ጥሪ በተደረገበት ጊዜ በከፋ ክ/ሀገር በጅማ ከተማ አገለግልበት ከነበረው የፖሊስ ሠራዊት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ግንባር ዘምቻለሁ፡፡*

*መጋቢት 28 ቀን 1978 ዓ.ም በግዳጅ ላይ ተመትቼ እጅግ ቆስዬ በነበረበት ወቅት፣ አብረውኝ ፍልሚያ ላይ የነበሩት ጓዶቼ ‹ጥቂት ቆይቶ ይሞታል› በማለት እያለቀሱ ወደፊት ትግላቸውን ቀጠሉ፡፡*

*በሠራዊቱ መካከል እየተንቀሳቀሱ ሲያዋጉ የነበሩት ጄኔራል ታሪኩ፣ ከሞቱ ጀግኖች ወንድሞቼ መካከል ነፍሴ እንዳልወጣችና በሥቃይ ላይ እንደነበርኩ ድንገት አይተው፣ በአስቸኳይ ትእዛዝ በቃሬዛ አስነሱኝ፡፡ በኋላም ለህክምና በሄሊኮፕተር ወደ አሥመራ እንድላክ አድርገዋል፡፡*

*ከተወሰነ ጊዜ በኋላም አሥመራ መጥተው ቁስለኞች ወታደሮችን እንደ ታላቅ ወንድም እየተዘዋወሩ ጠይቀውናል፡፡ በዚያን ጊዜ የእኔን ሁኔታ አይተውና በቂ እርዳታ እንዳልተደረገልኝ ሲረዱ፣ ወደ አዲስ አበባ በሄሊኮፕተር እንድወሰድ አዘው፣ በፖሊስ ሆስፒታል ታክሜና እግሮቼ ከመቆረጥ ድነው በሕይወት ቆሜያለሁ፡፡*

*ከሕይወቴ ጋር የተገናኘ በመሆኑ፣ በጥይት የተመታሁበትን አራተኛ ዓመት ሳከብር ለጄኔራል ታሪኩ የገጠምኳት ‹‹ታሪኩ ቋያ ነው›› የምትል የግጥም ማስታወሻ፣ ከዚህ በታች ያለችው ናት፡፡*

*መጋቢት 28 ቀን 1981 ዓ.ም*





## ‹‹ታሪኩ ቋያ ነው!!››

ከአበባው ከፍሌ

ታሪኩ ታሪክ ነው አይጠፋም ዘላለም
በደም የተጻፈ ያውም በቀይ ቀለም
መቃብሩ ጠፍቶ ቢበቅልበት አረም
ታሪኩ ቋያ ነው አይጠፋም ምንጊዜም፡፡

እንደ አንበሳ ደቦል ግርማው የሚያስፈራው
ቁጣው እንደ ነብር የሚንተከተከው
እናቱ ኢትዮጵያን ሲደፍሩ ከአየ ነው፡፡
የአባቱ ቴዎድሮስ ወኔ የወሰደው
የአባ ኵስትር በላይ ደሙ የነዘረው
አይዝግም ታሪኩ ምንጊዜም ሕያው ነው፡፡

በሰው ሠራሽ ሳይሆን በደሙ ጽፎታል
ታሪኩ ሲወሳ ለሁሌ ይኖራል፡፡
እንደ ገለባ እሳት ውስጡን ግሞ ግሞ
ታሪኩ ቦግ አለ በዘመን አርምሞ፡፡

ከትንሽዋ ኮዳ ቀድቶ በጋቤጣ
የቀዘቀዘውን ውሀ እንኳን ሳይጠጣ
ከቀበሮ ጉድጓድ አንድ ቀን ሳይወጣ
ኖሩ ከጦሩ ጋር እጅና ጓንት ሆነው
የግዳጅን ጫና ችግርን ተጋርተው፡፡

ከቆሰለው ቆስሎ ከደማውም ደምቶ
ጋሌጣ ቆርጥሞ ሙቅ ውሀ ጠጥቶ
የጠላት መሣሪያ ጭራሽ ሳይበግረው
ድሎትና ቆንጦት አቅድ ቀን ሳያምረው
የእናት ሀገር ወሰን፣ የእናት አገር ድንበር



ሁሉን አስተባብሮ አለቃና ምንዝር
በቆራጥ አመራር አስከብሮ ሲኖር
ምቀኞች ምንደኞች ስልታቸው የላቀ
በተንኮል ጠልፈውት በድንገት ወደቀ።

የአዘመተው መንግሥት፣
ሲገለው በጭፍን፣ ሲገለው በትዕቢት
የተወጋው ጠላት ‹ጀግና ወደቀ› አሉት
እጁን በእጁ በላ የኢሠፖ መንግሥት
የድንበሩን መዝጊያ ታሪኩን ሲገሉት።
ድምጺ ሀፋሽ ጣቢያም ጨፈረ በምፀት
በማለት አቅራራ፣
ማንም አይመክተን አሥመራ ለመግባት
ናደውም ተናደ በታሪኩ መጥፋት።
አውራ የሌለው ንብ ሆኖበት ነገሩ
ናደው ተበተነ በየሽንተረሩ።

---

*አበባው ክፍሌ ኃይሌ/ የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ*
*በአሁኑ ወቅት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።*





## ታሪክ ነው ታሪኩ!!

እንደ አምላክ ክርስቶስ፣
መከራ መስቀሉን፣ በግፍ ቢሸከምም
እንደ አቡነ ጴጥሮስ ታስሮ ቢረሸንም
የጨበጣት እውነት ሕያዊት ናትና
ትዘክረዋለች በትንሣኤ ፋና።

ዝናውን አጉድፈው
ውለታውን ነቅፈው
በጊዜ ክንዳቸው ቢጥሉትም ገፍተው
ተነስቷል ታሪኩ ገዳዮቹ ሞተው።

ጀግና በአካል ቢወድቅ ይነሣል በመንፈስ
የእውነት ልዕልና ስለማይገሰስ።
ሞት ቢገዳደረው ቢረታው አይሎ
ያበራል ታሪኩ መቃብር ፈንቅሎ።

*23ኛ የሙት ዓመት ለመዘከር በአዲስ አድማስ ጋዜጣ*
*የካቲት 7ቀን 2003 የታተመ፣*

## በደም የወረደ

ባህርይና ስሜት፣ ችሎታና ንቃት
ለሀገር ለወገን የመታመን ብቃት
የመልክ የቁመና የትውልድ ተዛምዶ
በረቂቃን ሕዋስ፣ ከደም ተዋህዶ፣ በዘር አስኳል ወርዶ
በውርስ ይከሰታል ደግሞ ተደጋግሞ
የቀደምት አባቶች፣ የቀደምት እናቶች፣
ወኔና ጀግንነት፣ መልክና ማንነት አይሞትም ፈጽሞ።

እንደተባረከ እንደ ንፁህ ስንዴ
ፍሬው ዘር ተክቶ ለምልሞ ዲነግዴ
ዛሬም በታሪክ አውድ ሕያውነት ለብሶ
በልጅ ልጆቹ ግብር ይወሳል በክብር፣ ጀብዱ ተንተርሶ።

እንደሚነገረው፣
በታሪክ አንደበት ትናንትናም ዛሬ
ዋቢ ነው ተምሳሌት በጀግንነት ሙያው የዲነግዴ ፍሬ።

ቃሉ እማይታበል ሥራው የነጠረ
የናደው ዕዝ አዛዥ ያለ፣ የነበረ
ጀኔራል ታሪኩ የንግርት ጀግና የአፋበቱ ፋና
አቋሙ  የጠራ፣ እምነቱ የፀና
እንደ ጀግና አጐቱ፣ የጦር ፊታውራሪ አባ መላ ሀብቴ
አጥርቶ ያወቀ ዕዝና አመራርን፣ የትግልን ሁናቴ

በጫጬ አስተሳሰብ በተንኮል ተጠልፎ
በሞት ከተለየን በጀግንነት አልፎ
ሃያ አምስት ዓመታት ነጕድ ተጓዙ
የታሪኩን ታሪክ ሳያደበዝዙ።





ከሀሰት፣ከሀሜት፣ከአናሳ አስተሳሰብ ፀንቶ የታገለ
ለእናት አገሩ ፍቅር፣ ሳመነበት ሙያው የተጕሳቆለ
የማዕዘን ደንጊያው፣የንግርት አንበሳ፣
ያ ጅግሣ ታሪኩ የዲነግዴ ፍሬ

ገለውት አልሞተም፣ ሙያው እያበራ፣
ህቅን ተመርኩዞ ቆሟል እስከዛሬ።

— · — · — ·

*በፀሐይ መልአኩ*
*የካቲት 7 ቀን 2005 ዓ.ም*
*ለ25ኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ*
*በአዲስ አድማስ ጋዜጣ የወጣ*

# የታሪክ ባለቤት፣ ጄኔራል ታሪኩ

ከቀበሮ ጉድጓድ ከበረሃ ኑሮ
አንድም ቀን ሳይወጣ ሁልጊዜም ተቀብሮ
በጦር ስልት አመራር በጀግንነት ሥራ
ውድ እናት አገሩን ወገኑን ያኮራ
የሚነገርለት ታሪክ በየመስኩ
አያሳዝንም ወይም ሲሆን ያለ መልኩ
የታሪክ ባለቤት ጄኔራል ታሪኩ።

በዕውቀት ያልበሰለ ኮሚኒስት ካድሬ
ጠልፎ ባቀረበው አሉባልታ ወሬ
እውነቱ ከሐሰት ነጥሮ ሳይለይ
በግፍ መወንጀሉ፣ በግፍ መገደሉ በሀገሩ ላይ
ፍትሕ የረገጠ፣ዐይን ያወጣ ድፍረት አልነበረም ወይ?

እንግዲህ አስተውሉ፣ ከዚያች ቅጽበት ኋላ
የሠራዊቱ ክንድ እንዴት እንደላላ።
ታሪኩ መሞቱ መውደቁ ሲወራ
የሚመክት ጠፋ ጠላት አንሠራራ።
ተስፋ የቆረጠው፣ በመሪው አሟሟት በዚያ የግፍ ሥራ
ሸሸ ሠራዊቱ ከየጦሩ ጉራ።



## በደም የወረደ

ባህርይና ስሜት፣ ችሎታና ኃቃት፣
ለሀገር ለወገን የመታመን ብቃት
የመልክ የቁመና፣የትውልድ ተዛምዶ
በረቂቃን ሕዋስ፣ ከደም ተዋህዶ፣
በዘር አስኳል ወርዶ

በውርስ ይከሰታል ደግሞ ተደጋግሞ
የቀደምት አባቶች፣የቀደምት እናቶች፣
ወኔና ጀግንነት፣ መልክና ማንነት
አይሞትም ፈጽሞ፡፡

እንደተባረከ እንደ ንፁህ ስንዴ
ፍሬው ተበራክቶ ለምልሞ ዲነግዴ
ዛሬም በታሪክ አውድ ሕያውነት ለብሶ
በልጅ ልጆቹ ግብር ይወሳል በክብር፣ጀብዱ ተንተርሶ፡፡



እንደሚነገረው፣
በታሪክ እንደበት ትናንትናም ዛሬ
ዋቢ ነው ተምሳሌት በጀግንነት ሙያው፣ የዲነግዴ ፍሬ፡፡
ቃሉ እማይታበል ሥራው የነበረ
የናደው ዕዝ አዛዥ ያለ፣ የነበረ
ጄነራል ታሪኩ፣ የአቶ ንግርት ልጅ፣የአፋቤቱ ፋና
አቋሙ የጠራ፣ ዕምነቱ የጸና፣
እንደ ጀግና አጎቱ፣ የጦር ፊታውራሪ
አባ መላ ሀብቴ
አጥርቶ ያወቀ ዕዝና አመራርን፣ የትግልን ሁናቴ
በሙት አስተሳሰብ በተንኮል ተጠልፎ
በሞት ከተለየን በጀግንነት አልፎ
ሃያ አምስት ዓመታት ነጕዱ ተኝዙ
የታሪኩን ታሪክ ሳያደበዝዙ፡፡

ከውሸት፣ ከሀሜት፣ ከአናሳ አስተሳሰብ ፀንቶ የታገለ
ለእናት አገሩ ፍቅር፣ ላመነበት ሙያው የተጕሰቆለ
የማዕዘን ደንጊያው፣ የአቶ ንግርት ልጅ፣
ያ ጅግሣ ታሪኩ፣ የዲነግዴ ፍሬ
ገድለውት አልሞተም፣ሙያው እያበራ፣
ሀቅን ተመርኩ፤ ቆሟል እስከዛሬ፡፡

በሀሰት በስብቀት በነገረ ሠሪ
የተወናበደው ያ ወፈፌ መሪ
በታሪኩ መሞት፣ ሥልጣኑ እንዳበቃ ኃይሉ እንደተናደ
ወዲያውኑ ሲያውቀው ተክለፍልፎ አበደ።
ገንጣይ በለስ ቀናው፣ ጠላት ተሞካሸ
በደንቆሮ አመራር የኢትዮጵያም ታሪኳ ጎድፎ ተበላሸ።

*በመጋቤ አዕላፍ መክብብ አጥናው ልዩ የአርበኞነት ባህርይ፣ ሲደመር ወታደራዊ ክሂል፣ ገጽ 70፣ መጋቢት 2004 ዓ.ም*





# *እወዳለሁ ጀግና*

*ሰሜቷን አጉኖ አግራሞቷን ሰቅሎ*
*እንዳንበረከካት ያ ጥቁር ኦቴሎ*
*እንደ ሼክስፒር ልጅ እንደ ዴዝዴሞና*
*ልቤ እስኪሰነጠቅ እወዳለሁ ጀግና::*

*እምነት ነው፣ ብቃት ነው፣ እውነት ነው ጀግንነት*
*የጥቂቶች ፀጋ የተፈጥሮ ውበት::*
*አደንቃለሁ ቆንጆ በክብሩ የሚያጌጥ*
*ስለሌሎች ጥቅም ሕይወቱን የሚሰጥ::*
*ፍቅሩ እማይበረዝ በዓላማው የፀና*
*መስዋዕትነቱ የሚታደግ ጀግና*
*ይኼ ነው ሰው ማለት በግል ሚዛኔ*
*ልቤ እስኪሰነጠቅ የምወደው እኔ::*

*የሰውነት ሚዛን ምግባሩ ነውና*
*ያከብረዋል ልቤ ይሆን ቅድስና::*
*መንፈሴን ያረካው የምርጫዬ ልኩ*
*ይህ ነው ውዴታዬ ሲገለጥ ታሪኩ::*

*'ከፀሐይ መልአኩ*
*የካቲት 1986 ዓ.ም.*

# ምዕራፍ ፲፬

## አይረሴ ጉዳይ

*ዛሬ ላይ የቆመ ነፃነት አጥልቶ*
*ከእግሩ ሥር ደም አለ፣*
*እንዳይረግጠው ንቆ።*









ሁሉን ቻይ ወገንህ ያልፋል ሲል ሲያቅማማ
መገደብ አቅቶት፣ የተውሣክ ወረርሽኝ፣ ታብቶ በፃማ
ሲነቀል ከቀዬው፣ ሲገፋ ሲሰደድ፣ ተርቦ ሲጠማ
ሲናጋ ከሥሩ የእሱነቱ ካስማ
ሥራን ካንተ ሊማር፣ ይናፍቅህ ገባ አሁን አሁንማ።

ሰብሳቢው ከዋኙ የሥራ ሰው ካሣ
ጠንቅ አነቃቀሉን ችግርና አበሳ
ሙያህን አስተምር እስቲ አንዴ ታነሣ።


# ምዕራፍ ፲፩

## አይረሴ ጉዳይ

ዛሬ ላይ የቆመ ነፃነት አጥልቆ
ከእግሩ ሥር ደም አለ፣
እንዳይረግጠው ንቆ።







ሁሉን ቻይ ወገንህ ያልፋል ሲል ሲያቅማማ
መገደብ አቅቶት፣ የተውሣክ ወረርሽኝ፣ ታብቶ በዓማ
ሲነቀል ከቀዬው፣ ሲገፋ ሲሰደድ፣ ተርቦ ሲጠማ
ሲናጋ ከሥሩ የእሱነቱ ካስማ
ሥራን ካንተ ሲማር፣ ይናፍቅህ ገባ አሁን አሁንማ።

ሰብሳቢው ከዋኙ የሥራ ሰው ካሣ
ጠንቅ አነቃቀሉን ችግርና አበሳ
ሙያህን አስተምር እስቲ አንዴ ታነሣ።



አቡነ ጴጥሮስ ጳጳስ
ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ



አቡነ ሚካኤል ጳጳስ
ዘ አዜበ ኢትዮጵያ

እኒህም ተቃጥለው በጥይት እሩምታ፣ በባሩድ ነበልባል
ለእውነት በሞገተው የእምነታቸው አስኳል
እንደ ጧፍ ሲነዱ ሆነው ብርሃን ፋና
አደራ አውርሰው ነው፣ ለተተኪው ትውልድ፣
ስለወገን ክብር የአገር ልዕልና፡፡

የእኒህን ታላቆች፣ ሰንደቅ ተምሳሌቶች፣ አደራ ማላላት
እርም ነው ሐራም ነው ቃላቸውን መብላት፡፡






## አገር ስትታጠር፣ አገር ስትሠራ
## እየተጋቱ ነው ግፍና መከራ፡፡



እጅና አንገታቸው ተቆርጦ፣
የፋሽት መዘባበቻ የሆኑት
የማይጨው ጀግና
ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም አባ ተጫን

1929 ዓ.ም.



ይህ ጀግና ሲሰዋ አደራ ትቶ ነው፡፡

*የሉዐላዊነት ድባብዋን ዘርግታ*
*አገር የቆመችው ክብርዋን ተጐናጽፋ፣ በነፃነት ኮርታ*
*ነፍስ ገብራ ነው፣ በልጆችዋ ነዲድ በእሳት ማዕበል ጋይታ*
*በደም ባህር ዋኝታ።*

---












*አገርን በአንድነት ያቆዩ ጀግኖች*
*አልጋ ወራሽ ተፈሪና ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ*



*የአፄ ምኒሊክ የጦር ሚኒስትር*
*ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ በጥንታዊው የማዕረግ ልብስ*





# አይመጣም አትበሉ

ድባቅ ገባ አትበሉ፣ ጠፍቷል ተደምስሶ
አይመጣም አትበሉ፣ ጠላት ተመልሶ
ዐመሉ ነውና ማድባት ቂሙን ነክሶ
መከሰቱ አይቀርም፣ የፋሽስት መንፈስ፣
በሰዎች ተዋርሶ፡፡

ሁኔታን መዋጀት ይገባል በአንክሮ
ራሱን ይደግማል ታሪክ ዞሮ ዞሮ፡፡
ይህን ጠንቅ ጉዳይ ለመንቀል ለማድረቅ
የጥንቱን መድኃኒት አንድ ሆኖ ማጽደቅ፡፡



የመጽሐፉ አዘጋጅ፣ ፀሐይ መልአኩ







መጽሐፉን በማስረጃ ያቀናበረችው
መቅደላ ታሪኩ

# ዋቢ መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ሰነዶች


ታደሰ ቴሌ ሰልባኖ፣ ም/ መቶ አለቃ፣ የአናብስት ምድር፣ አዲስ አበባ 1999 ዓ.ም.

ተስፋዬ ርስቴ፣ ሻምበል፣ ምስክርነት በባለሥልጣናቱ አንደበት፣ ግንቦት 2001 ዓ.ም

ዘነበ ፈለቀ፣ ነበር ክፍለ ሁለት፣ አዲስ አበባ ግንቦት 2001 ዓ.ም.

አምሳሉ ገብረዝጊ ገብሩ፣ ኰሎኔል፣ የኤርትራ መዘዝ፣ አዲስ አበባ ጥር 2002 ዓ.ም.

በጋለ ንጋቱ፣ ሻለቃ፣ ትውልድ ያናወጠ ጦርነት፣ አዲስ አበባ 2004 ዓ.ም

ዋስይሁን ንጋቱ፣ ብ/ጄኔራል፣ ዕጣ ፈንታና መስዋዕትነት፣ አዲስ አበባ መጋቢት 2005 ዓ.ም

የሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ቃለ ምልልስ፣ ሪፖርተር ሰኔና ሐምሌ እትም፣ቅጽ 7፣ ቁጥር 49፣ አዲስ አበባ 1995 ዓ.ም.

## ተጨማሪ ዋቢዎች፣

- የሻምበል መላኩ ፈረደ ደብዳቤ፣ 1985 ዓ.ም የተጻፈ፣
- የወታደር ሰለሞን ኢሣ ደብዳቤ፣ 1984 ዓ.ም የተጻፈ
- ከመቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ ጋር በ2002 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስና እንዲሁም የተበረከቱ ሰነዶች፣
- ከመከላከያ ሚኒስቴር የተወሰዱና በጄኔራል ታሪኩ የግል ፋይል ውስጥ የተገኙ ልዩ ልዩ ቀሪ ሰነዶች፣








በቋንቋ እግር ብረት፣ በቃላት ሰንሰለት
አበሻን ለማሰር በቅኝ ተገዥነት
የኮንት አንቶኖሊ የረቀቀ ወጥመድ፣የሸፍጥ ጨዋታ
በውሣኔሽ ሰይፍ ሥሩ ተቆረጠ፣ አንቀጽ 17 አገዳው ተመታ።

ዕብሪት ያነዘረው፣ብስጭት ያሾረው የሮማ ወታደር
እስከ አፍንጫው ታጥቆ፣ ሊያስገብር ሊወጋ፣ መጣ ሲንደረደር።
ዘለቀ መቀሌ፣ መከታውን ሠራ ምሽጉን መረገ፣ ካቡን አነባብሮ
መድፉን አንተራሰ በእሾህ ብረት አጥሮ።

ለዚህም ዘይደሽ ጣይቱ ቆራጥዋ፣ ብስል ብልሃተኛ
ጣሊያንን ፈጀሽው፣ በውሃ ጥም ጦርሽ ነቀልሽው ዳግመኛ።
ታሪክሽ ስንክሳር ትመስክር አድዋ፣
ትመስክር ሮምያ፣ አገርሽም ትናገር
ጣይቱ ጠሐይ ነሽ፣ ድል አዋላጂቱ፣ የማትጠልቂ ጀምበር።

2007ዓ.ም / ፀ.መ



ንቋ እግር ብረት፣ በቃላት ሰንሰለት



በግራና በቀኝ ከፊትና ኋላ፣ ኃይልህ ተዘርግቶ
በነራስ ጎበና፣ በነራስ መኰንን፣ በነራስ አሉላ፣ በነደጃች ሜጫ፣በጀግኖች ተሞልቶ
ሠራዊትህ ሲተም ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መውጫ
ብርድ ሳይበግረው ሳይረታው ረሞጫ
በወጣቱ ትንታግ በታፈሰ ዐባይነህ ወኔ በተሞላ
በአንድ ጕራዴ ምት 50 አንገት የቀላ
በበሻህ አቦዬ፣ ገበየሁ መድፈኛው
በባልቻ አባ ነፍሶ በሀብቴ መለኛው
ተከበህ ስትዘልቅ፣ በታላቅ ክብረ ኃይል ከሸዋ እስከ ትግሬ
የሮም ጄኔራሎች ዳቦርሜዳ፣ አርሞንዲ፣ አልቤርቶ፣ ኤሌና እነ ባራቶሬ
ብርክ ቢይዛቸው የፍርሃት ወጀቡ
እንደ ጃርት ፍልፈል ምሽግ ምሰው ገቡ።

በየካቲት ጊዮርጊስ በዚያ በቀውጢ ዕለት
ሃያ አምስት ሺህ ሰው ነፍሱን በሰዋበት
የዓለም ትውፊት እምነት፣ ታሪክ ፖለቲካ፣ ሲለወጥ ሲቀየር፣ ተአምር ሲፈነዳ
መሸጎ መች ቀረ፣ ረገፈ እንደ ቅጠል ጠላትና ባንዳ።

መንፈስ ጠንካራው እምዬ ምኒልክ
የሚመዘንብህ ጀግንነት የሰው ልክ
ዝንተ ዓለም ታሪክህ በዓለም ላይ ይወራ
ከሠራዊትህ ጋር ስምህ ደምቆ ይብራ።

2007ዓ.ም / ፀ.መ



ኛ ከፊትና ኋላ፣ ኃይልህ ተዘርግቶ




የካቲት 7 ቀን 1980 ዓ.ም በግፍ ለተገደሉት ለጀግናው
ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ
መታሰቢያ በደራሲት ፀሐይ መልአኩ የተሳለ ስዕል

* * *

‹‹...ጄኔራል ታሪኩ በግፍ ቢረሸንም፣ ለአገሩና ለወገኑ የከፈለው መስዋዕትነት፣ በቋሚ የታሪክ ምስክርነት፣ ስሙና ገድሉ ለዘለዓለም ሲዘከር ይኖራል፡፡ ይህ የታሪክ ሐቅ ስለሆነ ማንም ወይም ምንም ሊሽረው እና አፍኖ ሊያስቀረው አይችልም፡፡››

*ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን፣ 1995 ዓ.ም.*

ዋጋ 80 ብር

ሕትመት አልፋ አታሚዎች